# Dhimmoota horsiisee bultoota daangaa ce'an

## ድንበር ተሻጋሪ የአርብቶ አደሮች ጉዳዮች




**AKSHIIN FOOR DEVELOOPIMEENTII**

አክሽን ፎር ዴቨሎፕመንት

P.O.Box; 19859 afdethiopia@gmail.com

+251 011 662 59 76 www.afdethiopia.org

Addis Ababa, Ethiopia



**Produced by Action For Development with the support of Welthungerhilfe**

## Who We Are

Action For Development (AFD) is a local civil society organization registered with the FDRE Authority for CSOs, with certificate No. 0150. It became operational as an NGO in 1998.

## Our Vision

Empowered, resilient, and thriving citizens leading a dignified life in an enabling and sustainable environment.

## Our Mission

AFD is a learning organization, which in partnership with other development actors, complements the self-development initiatives of pastoral and other vulnerable communities in Ethiopia through undertaking programmes pertaining to resilient livelihoods, WASH and other basic services, natural resource management, social protection, DRM, and accountable governance, with the mainstreaming of such issues as gender transformation, Core Humanitarian Standard, capacity development, CCA, & youth empowerment.

## Our Objectives

The AFD programme, broadly, strives to contribute to the enhancement of:

- Food and nutrition security, and resilient livelihoods at the grassroots level
- Voice, space, and influence of deprived communities for the realization of citizen-responsive governance

## Our Key Thematic Areas of Engagement

- Resilient livelihoods.
- WASH and other basic social and economic services.
- Management and governance of natural resource.
- Social protection and disaster risk management.
- Civic engagement for accountable governance.

# Seensa

Hojiiwwan Action for Development hojjetu keessaa tokko mirga horsiisee bultootaa akka kabajamuf jecha hojiiwwan advookeesii imaammata jiranii irratti hojjechuu keessa isa tokko. Haaluma kanaan, ergaawwan advookesii kan waa'ee Horsiisee bultootaa fidhimmoota daangaa qaxxaamuran ilaalchisee ergaawwan advookesiiqophaa'aniiru. Ergaawwan kunnin bifa poostaraatiin maxxanfamanii horsiisee bultootaa fi qooda fudhattootaaf kan dhiyaatan yoo ta'u; Ergaawwan kana caalaatti ibsuuf barreeffamni gabaabaan kun mata dureewwan armaan gadii irratti xiyyeeffachuun qophaa'ee jira.

- Mootummaan seerota mijatoo baasuufi bu'uuraalee misooma gabaa babal'isuun daldala daangaa ce'uuf haala mijeessuu qaba,
- Sochii horsiisee bultootaafi beelladootasaaniif haala mijeessuun dirqama Mootummoota Biyyaalessaa fi Naannoleeti',
- Sirna itti fayyadama qabeenya uumamaa waloo daangaa ce'anii diriirsuun horsiise bultoonni nagaan akka waliin jiraataniif gumaacha guddaa qaba,
- Mootummaan waldhabdeewwan daangaa ce'an furuuf jecha sirnoota mala aadaa waldhabdee hiikuuf gargaaran fayyadamuufi beekamtii kennuufii qaba,
- Dhukkuboota daddarboo beelladootaa daangaa ce'an ittisuufi to'achuuf tumsiifi qindoominni barbaachisaadha,
- Rakkoowwan horsiisee bultootaa daangaace'oo furuuf qindoominniifi tumsi barbaachisaadha.

Poostaroonni ergaawwan of keessaa qaban bakkeewwan ifatti mul'achuu danda'anitti erga maxxanfamanii booda hojjettoonni misoomaa ykn warri ergaa sana dabarsuu barbaadan barreeffama kana fayyadamuun ergaawwan abukaatummaa caalaatti hubachuu fi ibsuu ni danda'u.

# መግቢያ

አክሽን ፎር ዲቨሎፕመንት ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል የአርብቶ አደሮች መብቶች እንዲከበሩ አላማ ያደረገ የፖሊሲ አድቮኬሲ ስራ አንዱ ነው። በዚህም መሰረት የአድቮኬሲ መልዕክቶች አርብቶ አደሮችን ከሚመለከቱ ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች ጋር ተያይዘው ተዘጋጅተዋል። እነዚህ መልዕክቶች በፖስተር መልክ ታትመው ለአርብቶ አደሮችና ለባለድርሻ አካላት የቀረቡ ሲሆን ፤ መልዕክቶቹንም የበለጠ ለማብራራት የሚከተሉት አርዕስቶች ላይ ትኩረት አድርጎ ይህ አነስተኛ ጽሁፍ ተዘጋጅቷል።

- መንግስት ተገቢውን ህጎች በማውጣትና የገበያ መሰረተ ልማት በማስፋፋት ድንበር ተሻጋሪ ንግድን ማሳለጥ አለበት፣
- የአርብቶ አደሮች እና የእንስሶቻቸውን እንቅስቃሴን ማሳለጥ የሀገራዊና ክልላዊ መንግስታት ግዴታ ነው፣
- ድንበር ዘለል የተፈጥሮ ሀብትን በጋራ የመጠቀም ስርአት መዘርጋት ለአርብቶ አደሮች በሰላም አብሮ ለመኖር ትልቅ አስተዋጽዎ ያበረክታል፣
- መንግስት ድንበር ዘለል ግጭቶችን ለመፍታት የባህላዊ ግጭት መፍቻ ስርአቶችን መጠቀምና እውቅና መስጠት አለበት፣
- ድንበር ተሻጋሪ ተዛማች የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ትብብርና ቅንጅት ያስፈልጋል፣
- ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ የአርብቶ አደሮችን ችግሮች ለመፍታት ቅንጅትና ትብብር ያስፈልጋል።

መልዕክቶቹን የያዙት ፖስተሮች በግልጽ ሊታዩ በሚችሉ ቦታዎች ላይ ከተለጠፉ በኋላ የልማት ሰራተኞች ወይም መልዕክቱን ለማስተላለፍ የሚፈልጉ አካላት ይህንን ጽሁፍ በመጠቀም በአድቮኬሲ መልዕክቶቹ ላይ የተሻለ ግንዛቤ ለማስጨበጥና ገለጻ ለማድረግ ይችላሉ።

# 1. Mootummaan seerota mijatoo baasuufi bu’uuraalee misooma gabaa babal’isuun daldala daangaa ce’uuf haala mijeessuu qaba.

መንግስት ተገቢውን ህጎች በማውጣትና የገበያ መሰረተ ልማት በማስፋፋት ድንበር ተሻጋሪ ንግድን ማሳለጥ አለበት።



Daldalli daangaa ce’un/qaxxaamuruun aanaalee daangaatti taasifamu hawaasa naannawichaatiif wabii nyaataa ta’uun, galii maddisiisuun, akkasumas carraa hojii uumuuf murteessaadha. Waliigaltee daldala Itoophiyaafi Keeniyaa hojiirra oolchuuf qajeelfamni bahe,daldala xixiqqaa daangaa ce’u ji’atti hanga qarshii kuma digdamaa (20,000) ga’u meeshaalee qajeelfama kana keessatti tarreeffamaniif ni eeyyama.

Haa ta'u malee daldalli eeyyamame kun hangi baay’ina qarshiisaa xiqqaachuutti dabalee yeroo dheeraaf dhorkameera. Kanamalees labsiin gabaa beelladaa lak. 819/2014 beelladoota wiirtuu daldalaa seeraan tumameen ala gurguruu kan dhorke yoo ta’u, seerichi yoo sarbame beellada dhaaluufi adabbii hidhaa akka dabalatu kaa’a. Gama biraatiin seeronni gumurukii Itoophiyaa meeshaalee hinbeekamne biyyaa gara alaattis ta'ee alaa gara biyyaatti sochoosuu yakka taasisu.

Sababuma kanaan daldalli daangaa qaxxaamuruufi naannawichatti mul’atu idilee akka hintaaneefi seeraan ala akka ta’etti ilaalama. Dabalataanis, nageenya dhabuun, ittifayyadama bu’uuraalee misooma gabaa dadhabaa ta’eefi utuu to’annoo sirrii jalatti hinhammatamin kan raawwatamuudha. Mootummoonni biyyoota lamaanii

waliigalteewwan faayidaa daldalli daangaa qaxxaamuru hawaasa horsiisee bulaaf qabu tilmaama keessa galchanii walii mallatteessuun foddaa daldalaa addaa mijeessuufi bu’uuraalee misooma gabaafi tajaajila barbaachisu guutuu qabu.

በድንበር አካባቢ የሚካሄደው የድንበር ተሻጋሪ ንግድ ለአካባቢው ማህበረሰብ የምግብ ዋስትና፣ ገቢ ማስገኛ እንዲሁም ለስራ እድል ፈጠራ ወሳኝ ነው። የኢትዮጵያና የኬንያ ንግድ ስምምነትን ለማስፈጸም የወጣው መመሪያ በወር እስከ 20,000 ብር የሚደርስ ድንበር ዘለል አነስተኛ ንግድ በመመሪያው ውስጥ ለተዘረዘሩ እቃዎች ይፈቅዳል። ይሁን እንጂ የተፈቀደው ንግድ የገንዘብ ጣሪያ ከማነሱም በላይ ይህ ንግድ ለረዥም ጊዜያት ታግዶ ይገኛል። በተጨማሪም የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁ. 819/2014 እንስሳትን በህግ በተደነገገው የገበያ ማዕከል ካልሆነ በስተቀር መሸጥ የከለከለ ሲሆን ለጥሰቱ እንስሳውን መውረስ እና እስራትን የጨመረ ቅጣቶችን ያሰቀምጣል። በሌላ በኩል የኢትዮጵያ የጉምሩክ ሕጎች ያልታወቁ ዕቃዎችን ከአገር ወደ ውጭም ሆነ ወደ አገር ውስጥ ማዛወርን ወንጀል ያደርጋሉ።

በነዚህ ምክንያቶች በአካባቢው የሚስተዋለው የድንበር ተሻጋሪ የንግድ እንቅስቃሴ መደበኛ ያልሆነ እና ህገወጥ ተደርጎ የሚታሰብ ነው። በተጨማሪም በጸጥታ ችግር፣ በደካማ የግብይት መሠረተ ልማት ተጠቃሚነት እና በተገቢው የቁጥጥር ማዕቀፍ አለመኖር ታጅቦ የሚፈጸም ነው። የሁለቱ ሀገራት መንግስታት ድንበር ተሻጋሪ ንግድ ለአርብቶ አደር ማህበረሰቦች ያለውን ጥቅም ግምት ውስጥ ያስገቡ ስምምነቶች በመፈራረም ለድንበር ተሻጋሪ ንግድ ልዩ የግብይት መስኮት ማመቻቸት እና የገበያ መሰረተ ልማትና አገልግሎት ማሟላት አለባቸው።

## 2 . Sochii horsiisee bultootaafi beelladootasaaniif haala mijeessuun dirqama Mootummoota Biyyaalessaa fi Naannoleeti.

የአርብቶ አደሮች እና የእንስሶቻቸውን እንቅስቃሴን ማሳለጥ የሀገራዊና ክልላዊ መንግስታት ግዴታ ነው።



Fedhiiwwan bu'uuraa horsiisee bultoota naannawa daangaatti argamaniif barbaachisoo ta'an keessaa tokko sochii beelladoota saanii daangaa hinqabneedha.

Abbaan Taayitaa Tumsa Misooma Mootummoota Afriikaa Bahaa ('IGAD) ALA bara 2020tti sochii bilisaa, nageenyisaa eegame beelladoonniifi horsiisee bultoonni daangaa ce'anii dheedichaafi bishaan barbaachaaf taasisan to'achuuf kaayyeffatee **Pirotokolii Tiraansihumansi raggaasiseera**. Pirotokoliin kun biyyoonni miseensa ta'an sochii daangaa qaxxaamuraa waqtaawaa kana, akka bifa jireenya horsiisee bulaa tokkootti lakkaa'uun beekamtiifi eeyyama akka kennaniif dirqama kaa'a.

Sochiin bilisaa beelladootaafi horsiisee bultootaa sababa cufamuu daangaafi dhorka ittifayyadama qabeenya uumamaatiin dhiibbaan irra dhaqqaba. Walmorkiifi dorgommiin gosoota gidduu jiru hanqina naamusa gaarii waliin walitti dabalamee saamicha looniifi daangeffamuu sochiitiif sababa ta'aa jira. Kanaafuu, mootummaan federaalaafi naannoo rakkoolee kanneen hiikuun akka sochiin horsiisee bultootaafi beelladaa hindaangeffamneef haala mijeessuun dirqamasaanii bahachuu qabu.

የድንበር አካባቢ አርብቶ አደሮች ከሚያስፈልጓቸው መሰረታዊ ነገሮች አንዱ ለከብቶቻቸው ያልተገደበ ድንበር ተሻጋሪ እንቅስቃሴ ነው። የምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት ባለስልጣን (ኢጋድ) ነፃ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ ለግጦሽ እና ውሃ ፍለጋ የሚካሄድ የእንስሳትና አርብቶ አደሮች ድንበር ተሻጋሪ እንቅስቃሴን ለማስተዳደር አላማ ያደረገ **የትራንስሂማንስ ፕሮቶኮል እ.ኢ.አ በ2020 ዓ.ም አፀድቋል**። ፕሮቶኮሉ አባል ሀገራት ይህን መሰል ወቅታዊ የድንበር ተሻጋሪ እንቅስቃሴ እንደ አርብቶ አደሮች የኑሮ ዘዴ ቆጥረው እውቅና እንዲሰጡና እንዲፈቅዱ ግዴታ ያስቀምጣል።

ነጻ የእንስሳትና የአርብቶ አደሮች እንቅስቃሴ በድንበሮች መዘጋት እና በተፈጥሮ ሃብት የመጠቀም ክልከላዎች አሉታዊ ተጽዕኖ ይደርስበታል። በጎሳዎች መካከል ያለ ፉክክርና ባላንጣነት ከስነ-ምህዳራዊ እጥረት ጋር ተዳምሮ ለከብቶች ዘረፋ እና ለእንቅስቃሴ መገደብ ምክንያት እየሆነ ነው። በመሆኑም ሀገራዊና ክልላዊ መንግስታት እነዚህን ችግሮች በመፍታት ያልተገደበ የአርብቶ አደሮች እና የእንስሳት እንቅስቃሴን የማሳለጥ ግዴታቸውን መወጣት አለባቸው።

## 3 . Sirna itti fayyadama qabeenya uumamaa waloo daangaa ce’anii diriirsuun horsiise bultoonni nagaan akka waliin jiraataniif gumaacha guddaa qaba.

ድንበር ዘለል የተፈጥሮ ሀብትን በጋራ የመጠቀም ስርአት መዘርጋት ለአርብቶ አደሮች በሰላም አብሮ ለመኖር ትልቅ አስተዋጽዎ ያበረክታል።



Hawaasni horsiisee bultoonni naannawa daangaa jiran, bu’uura aadaafi sirna bartee bulchiinsa lafaasaaniitiin, albuudota uumamaan argamaniifi tajaajila nyaata beelladasaaniif oolan kanneen akka marga dheedichaa, bishaaniifi soogidda amoolee loon gaanfaa waliin fayyadamu.

Waliigalteewwan qoodiinsaafi tumsaa kunniin kan jijjiiramaniifi yeroo yeroon fooyyeeffaman yoo ta’u, garee miseensa ta’e tokkoof akkuma haalasaatti raawwatamuuf. Taateewwan tokko tokko keessatti gareewwan horsiisee bultootaa qabeenya uumamaa tokkoof utuma mirga qabiyyummaa seeraa qabanii gareewwan biroo akka ittifayyadamaniif nimari’atu. Haala kanaan aadaan qabeenya daangaa ce’anii argaman kanneen akka bishaaniifi marga dheedichaa karaa nagaan ittifayyadamuu guddateera.

Sirni hirmaachisaafi mala biyya keessaatiin qabeenya uumamaa waliin qooddachuu kun gareewwan horsiisee bultootaa daangaa ce’an gidduutti nagaan akka jiraatu taasiseera. Kanaafuu, sirna hirmaachisaafi mala biyya keessaatiin qabeenya uumamaa daangaa ce’an waliin fayyadamuu diriirsuun, nagaa waliin jireenya horsiisee bultootaaf gumaacha olaanaa waan qabuuf cimuufi beekamtii argachuu qaba.

በድንበር አካባቢ ያሉ የአርብቶ አደር ማህበረሰቦች በባህላቸውና የዘልማድ መሬት አስተዳደር ስርአታቸው መሰረት ለእንስሳት መኖ አገልግሎት የሚውሉ እንደ ግጦሽ፣ ውሃ እና የቀንድ ከብቶች የሚልሷቸውን እንደ ጨው አይነት በተፈጥሮ የሚገኙ ማዕድናትን በመጋራት ይጠቀማሉ። እነዚህ የመጋራት ስምምነቶችና ትብብሮች ተለዋዋጭ እና በየጊዜው የሚሻሻሉ ሲሆን አባል ለሆነ አንድ ቡድን እንደ ሁኔታው ይፈጸማሉ።

በአንዳንድ አጋጣሚዎች የአንድን ተፈጥሮ ሀብት ህጋዊ ይዞታ የያዙ የአርብቶ አደር ቡድኖች ሌሎች ቡድኖች እንዲጠቀሙበት ድርድር ያደርጋሉ። በዚህም አሰራር እንደ ውሃ እና ግጦሽ ያሉ ድንበር ተሻግረው የሚገኙ ሀብቶችን በሰላማዊ መንገድ በጋራ የመጠቀም ባህል ዳብሯል።

ይህ አሳታፊና ሀገር በቀል የተፈጥሮ ሀብት የመጋራት ስርዓት በድንበር ዘለል አርብቶ አደር ቡድኖች መካከል ሰላማዊ አብሮነት እንዲኖር አስችሏል። ስለዚህ አሳታፊና ሀገር በቀል ድንበር ተሻጋሪ የተፈጥሮ ሀብትን በጋራ የመጠቀም ስርአት መዘርጋት ለአርብቶ አደሮች ሰላማዊ አብሮ መኖር ትልቅ አስትዋጽዎ ስለሚያበረክት ሊጠናከርና እውቅና ሊሰጠው ይገባል።

# 4. Mootummaan waldhabdeewwan daangaa ce’an furuuf jecha sirnoota mala aadaa waldhabdee hiikuuf gargaaran fayyadamuufi beekamtii kennuufii qaba.

መንግስት ድንበር ዘለል ግጭቶችን ለመፍታት የባህላዊ ግጭት መፍቻ ስርአቶችን መጠቀምና እውቅና መስጠት አለበት።



Walittibu'iinsi gosaafi jeequmsi, hawaasa horsiisee bulaa naannawa daangaa Keeniyaafi Itoophiyaa jiran hirmaachise darbee darbee nimudata. Waldhabdeen akkanaa saamicha loowwan gaanfaaf, mancaatii qabeenyaaf, du'a lubbuu namootaatiif, gaaga'ama xiinsammuuf akkasumas sosochii daangessuuf oggaa sababa ta'u mul'ata.

Meeshaan waraanaa naannawichatti babal'achuun waldhabdeewwan kunneen lubbuu akka galaafataniifi rakkoon akka hammaatu taasiseera. Waldhabdeen gosoota daangaa ce'anii yeroo baay'ee kan ka'uufi babal'atu sababa walmorkiifi waldorgommii gidduusaaniitti uumamuun, saamicha looniitiin akkasumas sababoota dinagdeefi uumamaa adda addaarraa kan ka'eedha.
Haalli qilleensaa yeroorraa gara yerootti hammaachaa dhufuufi fedhiiwwan aadaan ala ta'an dantaaleen siyaasaafi dinagdee adda addaas, babal'achuu waldhabdee kanneeniitiif sababa ta'aa jiru.
Malli baratamaan naannawichatti waldhabdeen ittiinhiikamu hawaasa gidduutti haasawa nagaa taasisuufi walitti bu'iinsa jaarsummaadhaan hiikuurratti kan hundaa'eedha. Maloonni waldhabdeewwan ittiinhiikaman kunneen dhaabbilee mootummaafi mitmootummaa kanneen biyyaalessaafi idiladdunyaatiin deeggaramuufi jabeeffamuu qabu.
Kana malees, walittibu'iinsa ittisuu, hir'isuufi to'achuuf qaamoleen mootummaa sadarkaa sadarkaan

jiran sirna aadaa waldhabdeen ittiinhiikamu fayyadamuufi beekamtii kennuufi qabu. Mootummaan naannoowwan daldalli meeshaa waraanaa seeraan alaa adeemsifamurrattis tarkaanfii fudhachuufi sirna bulchiinsa gaarii diriirsuu qaba.

በኬንያ እና ኢትዮጵያ ድንበር በኩል ያሉትን የአርብቶ አደር ማህበረሰቦችን የሚያካትት የጎሳ ግጭት እና ሁከት አልፎ አልፎ ይከሰታል። እንዲህ ያለ ግጭት ለቀንድ ከብቶች መዘረፍ፣ ለንብረት መውደም፣ ለሰዎች ሞት፣ ለስነልቦናዊ ቀውስ እና ለእንቅስቃሴ መገደብ ምክንያት ሲሆን ይስተዋላል። በአካባቢው የጦር መሳሪያዎች መስፋፋት እነዚህን ግጭቶች ገዳይ እና አስከፊ አድርጓቸዋል። የድንበር ተሻጋሪ ጎሳዎች ግጭቶች ብዙውን ጊዜ የሚቀሰቀሱትና የሚስፋፉት በጎሳዎች መካከል ባለ ፉክክርና ባላንጣነት፣ በከብቶች ዝርፊያ እና በተለያዩ የኢኮኖሚያዊና ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ነው። በተጨማሪም የአየር ንብረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ መምጣትና የተለያዩ ባህላዊ ያልሆኑ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶች ለነዚህ ግጭቶች መስፋፋት ምክንያት እየሆኑ ነው።

በአካባቢው ያለው የተለመደ የግጭት አፈታት ዘዴ በማኅበረሰቦች መካከል የሰላም ንግግሮችን በማድረግና ግጭቶችን ያለሁከት በሽምግልና መፍታት ላይ የተመሰረተ ነው። እነዚህ የግጭት አፈታት ዘዴዎች በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ አለም አቀፍና ሀገር በቀል ተቋማት መደገፍና መጠናከር አለባቸው። በተጨማሪም ግጭቶችን፣ ለመከላከል፣ ለመቀነስና ለማስተዳደር በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የመንግስት አካላት የባህላዊ ግጭት መፍቻ ስርአቶችን መጠቀምና እውቅና መስጠት አለባቸው። ከዚህ በተጨማሪም መንግስት በአካባቢው ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ንግድና ዝውውርን የሚከለክሉ እርምጃዎችን መውሰድና መልካም አስተዳደርን ማስፈን ይኖርበታል።

## 5. Dhukkuboota daddarboo beelladootaa daangaa ce’an ittisuufi to’achuuf tumsiifi qindoominni barbaachisaadha.

ድንበር ተሻጋሪ ተዛማች የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር
ትብብርና ቅንጅት ያስፈልጋል።



Naannawawwan daangaa Itoophiyaafi Keeniyaatti dhukkuboonni daddarboon beelladootaa daangaa ce’an hawaasa horsiisee bultootaarratti miidhaa guddaa geessisu. Biyyoonni kunneen yoo waliin ta’anii dhibeewwan daangaa ce’an ittisuufi to’achuu dadhaban, horsiisee bultoonni bishaaniifi marga dheedichaa barbaacha iddoo tokkoo gara biraatti waan socho’aniif dhibeewwan tasa muudatan omishtummaafi baay’ina beelladootaarratti miidhaa guddaa dhaqqabsiisaa jiru. Dhiibbaan bu’uura jireenya horsiisee bultootaarratti geessisan cimaadha.

Biyyi tokko beellada gamasaatiin jiran qofaaf talaallii kennee yoo dhiiseefi, gama biraatiin bifa walfakkaatun beelladoonni yoo hintalaalchifamne, beelladoonni biyya tokkoo gara biyya biraatti waan socho’aniif tatamsa’ina dhukkubootaa to’achuun hindanda’amu.

Kana malees tajaajilli fayyaa beelladootaa dadhabaan jiraachuufi sirna gabaasa dhukkubootaarratti biyyoota lamaan jidduutti qindoominni jiraachuu dhabuun naannawa daangaatti tatamsa’ina dhukkuboota beelladaa dabaluun hawaasa horsiisee bulaa miidhaa jira. Kanaafuu, biyyoonni lamaan dhibeewwan daddarboo beelladootaa ittisuufi to’achuuf waliigalteewwan daangaa ce’an hojiirra oolchuun tumsaafi qindoominaan hojjechuu qabu.

በኢትዮጵያና በኬንያ ድንበር አካባቢዎች ድንበር ተሻጋሪ ተዛማች የእንስሳት በሽታዎች በአርብቶ አደር ማህበረሰቦች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላሉ። እነዚህ አገራት ተቀናጅተው ድንበር ተሻጋሪ በሽታዎችን በጋራ መከላከልና መቆጣጠር ካልቻሉ አርብቶ አደሮች ግጦሽና ውሃ ፍለጋ ከቦታ ወደቦታ መንቀሳቀሳቸውን ተከትሎ በድንገት የሚከሰቱ በሽታዎች የእንስሳት ምርታማነትና ቁጥር ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ ይገኛል። እንዲሁም የአርብቶ አደሮች የኑሮ መሰረት ላይ ጫና ያደርሳሉ።

አንዱ ሀገር በራሱ በኩል ያሉትን እንስሳት ብቻ ከትቦ ቢተውና በሌላኛው በኩል በተመሳሳይ እንስሳቱ ባይከተቡ፣ እንስሳቱ ከአንዱ አገር ወደሌላኛው ስለሚንቀሳቀሱ የበሽታዎቹን ስርጭት መቆጣጠር አይቻልም።

ከዚህ በተጨማሪ ደካማ የእንስሳት ህክምና አገልግሎት መኖርና እና በበሽታዎች ሪፖርት/መረጃ ስርአቶች ላይ የሁለቱ ሀገራት ቅንጅት አለመኖር በድንበር አካባቢ የእንስሳት በሽታ ስርጭትን በመጨመር የአርብቶ አደር ማህበረሰቦች ላይ ጉዳት እያስከተለ ይገኛል። በመሆኑም ሁለቱ ሀገሮች የእንስሳት ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የድንበር ዘለል ስምምነቶችን በመፈጸም በትብብርና በቅንጅት መስራት አለባቸው።

## 6. Rakkoowwan horsiisee bultootaa daangaace'oo furuuf qindoominniifi tumsi barbaachisaadha.

ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ የአርብቶ አደሮችን ችግሮች ለመፍታት ቅንጅትና ትብብር ያስፈልጋል::



Daangaan Keeniyaafi Itoophiyaa addaan baasu fageenya kiiloo meetira 600 ol kan dheeratu yoo ta'u, ummanni naannawaa daangaa biyyoota lamaanii keessa jiraatu eenyummaa ittiin adda baafamu kan sabummaa, aadaafi amantaa walfakkaatu kan qaban yoo ta'u, jireenya horsiisee bulaafi gariin horsiisee bulaa ta'e kan hordofaniidha.

Naannawa kanatti tajaajilli hawaasummaafi bu'uuraaleen misoomaa biroon haala gahaa ta'een kan hin jirreefi hiyyummaan bal'inaan kan ittimul'atuudha. Kana malees gogiinsi sababa jijjiirama qilleensaatiin dhufu, miidhaannaannawa uumamaa, walittibu'iinsi gosaafi sochiin horsiisee bultoonniifi beelladoonnisaanii taasisaniifi kkf hedduun mallattoolee hawaasummaa naannawichaati.

Rakkoolee kanneen furuuf hawaasni daangaa waloorratti argamu aadaa, dhaabbileefi beekumsa ofiitti fayyadamuun rakkoolee waloosaanii walumaan hiikuuf, kennaa uumamni hirpheef waliin fayyadamuuf yaalu.

Haa ta'u malee sirnoonni aadaa kunneen qaamolee mootummaa dhimmi ilaallatuun utuu beekamtii gahaa hinargatin turaniiru.Kanaafuu, jireenya ummata naannawa daangaa jiraatanii fooyyessuuf hojiiwwan misoomaa bu'uura duudhaa aadaasaaniirratti hundaa'uun hojjetamuu qabu.Bu'aqabeessummaa hojiiwwan kanneniitiif tumsiifi qindoominni mootummoota ollaafi dhaabbilee dhimmi ilaallatu biroo barbaachisaadha.

ኬንያ እና ኢትዮጵያን የሚለያየው ድንበር ከ600 ኪሎ ሜትር በላይ ርዝመት ሲኖረው በሁለቱ ሀገራት አዋሳኝ አካባቢዎች የሚኖሩ ህዝቦች ተመሳሳይ የብሄር፣ የባህል እና የሃይማኖት መለያዎች ያላቸው እና አርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ህይወት የሚከተሉ ናቸው። ይህ አካባቢ የማህበራዊ አገልግሎቶች እና ሌሎች የመሰረተ ልማቶች በበቂ ሁኔታ የሌሉበትና ድህነት በከፍተኛ ደረጃ የተንሰራፋበት ነው። ከዚህ በተጨማሪ የአየር ፀባይ መለዋወጥ የሚያመጣው ድርቅ፣ የተፈጥሮ አካባቢ መጎዳት፣ የጎሳ ግጭት እና የአርብቶ አደሮችና የእንስሶቻቸው እንቅስቃሴን መገደብን ጨምሮ በርካታ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የእነዚህ አካባቢዎች መገለጫ ናቸው።

እነዚህ ችግሮች ለመፍታት በጋራ ድንበር ላይ የሚገኙ ህብረተሰቦች ባህሎቻቸውን፣ ተቋማቸውንና እውቀታቸውን በመጠቀም የጋራ ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታትና ተፈጥሮ ያደለቻቸውን ፀጋ በጋራ ለመጠቀም ጥረት ያደርጋሉ። ይሁንና እነዚህን ባህላዊ ሰርዓቶች በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በቂ እውቅና ሳያገኙ ቆይተዋል። ስለዚህ የድንበር አካባቢ ህብረተሰቦችን ህይወት ለማሻሻል እነሱን ያማከሉና በባህላዊ እሴቶቻቸው ላይ የተመሰረቱ የልማት ሰራዎች መከናወን ይኖርባቸዋል። ለነዚህ ስራዎች ውጤታማነት የአጎራባች መንግስታትና ሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት በትብብርና በቅንጅት መስራት ወሳኝነት አለው።


Action For Development
19859
+251 011 662 59 76
E-mail; afdethiopia@gmail.com
Addis Ababa, Ethiopia
Stay connected